# ሳቀብን ድጋሚ



ቲሪሪም ፤ ቲሪሪም ፤ ቲሪሪም ፤ ባልነበር
ወያኔ ዘንድሮ ፤ መቀበሪያው ነበር ።

ግና ምን ያደርጋል ፤ እነ ያአደረ አፋሹ
በውርዴ ተማርኮ ፤ አፋሽ አጎንባሹ
ካባቱ ገዳይ ጋር ፤ አንድ ማዕድ ጎራሹ
ተነካሁኝ ብሎ ፤ ነጋ ጠባ አልቃሹ
የቀድሞ ወያኔን ፤ አዝለው ሲያቀረሹ
በኩርኩም ተነድሎ ፤ ሄዶ ጫማ ላሹ
ወያኔን ሳያውቁት ፤ በከንቱ ሲታሹ
የህዝባዊን አመፅ ፤ መንገድ ሲያበላሹ
በካርድ እንደማይሄድ ፤ ተሰጠ ምላሹ
ዳግመኛ ዘንድሮም ፤ ትግሉን አኮላሹ ።

ተለማምጦ አዳሪ ፤ ትግልን አዘጋሚ
ገሎ እንደመጨረስ ፤ ጠጋኝ አስታማሚ
የቆሰለ እንዳይሞት ፤ ተረዳድቶ አካሚ
እንኳን ደስ አላችሁ ፤ ስመ ተቃዋሚ
ያሜሪካው ሎሌ ፤ ያውሮፓው ከዳሚ
ያረብ ተላላኪ ፤ ትንቧሀም ፤ ጫት ቃሚ
ምስጋና ለናንተ ፤ ሊሆን ነው ከራሚ
አጋሰስ ወያኔ ፤ ሳቀብን ድጋሚ ።

ታዛቢው … May 24, 2010